# ግንባር ወይስ አሃዳዊ ፓርቲ?

"እንኳንም የህወሓት/ኢህአዴግ ልጆች ሆን"

ብርሃኔ በርሂ

05-05-16

ከዓመታት በፊት ነዉ። በ1994።በተማሪነት ዘመን። በወቅቱ "የኢትዮጵያና ሱዳን ግንኙነት ድህረ 1983፦ግጭት፤ትብብርና መጻኢ ተስፋ" የተሰኘች የጥናት ወረቀት ቢጤ ለማዘጋጀት መጻህፍት ማገላበጥ ያስፈልግ ነበር። በህንዳዊ ጋዜጠኛ የተጻፈ መጽሀፍ ተገኘ። ትኩረቱን ያደረገዉ በአፍሪካ ቀንድ ግጭቶችና መንስኤዎቻቸዉ ላይ ነዉ። መጽሃፉ።በቀዝቃዛዉ ጦርነት ሳቢያ ሁለቱም ጽንፎች(ፖላሮች) የአፍሪካ ቀንድ ሀገራትን ለመቀራመት ባደረጉት የጣልቃገብነት ሽሚያ ለግጭቶቹ መባባስ ምክንያት ስለመሆናቸዉ በአግባቡ ተብራርቷል። የወቅቱን የአፍሪካ ቀንድ መንግስታት ባህሪያትንም አብጠርጥሮ ተንትኗል። በመጽሃፉ አንድ አንቀጽ ላይ የሰፈረዉ መረጃ ግን የማገመት ነበር። ቃልበቃልም ባይሆን የጽሁፉ ይዘት እንዲህ ይነበባል። "መንግስቱ ሀይለማሪያም እስከወዲያኛዉ እንደጦር እንዲፈራ ምክንያት የሆነበት አንድ የታሪክ አጋጣሚ ተከስቶ ነበር። ወደተደላደለ ስልጣን ለመምጣት በጅምር ላይ እንዳለ በአንድ ወቅት አንድ ደፋር አጋጠመዉ። ሰዉየዉ አገር ሰላም ነዉ ብሎ እርሳቸዉን የሚቃረን ሀሳብ ጨምሮ እንደልቡ ተናገረ። አጅሬ መንግስቱ ይህን ነጻነትና ድፍረት የተሞላበት ንግግር ከዚያች እለት በኋላ በማንም ሰዉ እንዳይደገም የማስጠንቀቂያ ደወል

መደወል ነበረባቸዉ። በመሆኑም ሽጉጣቸዉን ስበዉ በተናጋሪዉ ጓዳቸዉ ግንባር ላይ ያለርህራሄ እንደመብረቅ አበራበት። ከዚያን ጊዜ ወዲህ መንግስቱ የሚባል ፍጡር እንደአዉሬ ይፈራ ጀመር። ያቺ ቀን የፍጹም አንባገነንነቱ ቀይ መስመር ሆነች።...ከዚያ ወዲህ የሰዉ አዉሬ ሆነ ይባላል....” ይላል ይዘቱ።

## *ከህወሓት የተማርኩት ስነምግባርንና ግዴታዬንም ጭምር ነዉ*

እኛ ደግሞ የመንግስቱ ወይም የደርግ ሳንሆን የህወሓት/ኢህአዴግ ልጆች ነን። ህወሓት የቀረጸንና ያስተማረን። ከህወሓት ነጻነትንና መብትን እንጂ ፍርሃትን አልተማርንም። አጎብዳጅነትና አሽቃባጭነት አጠገባችን እንዳይደርስም አጠንክሮ አስተምሮናል-ህወሓት። ከወላጆቻችን ቀጥሎ ስብእናችን በአግባቡ የተቀረጸዉ በህወሓት ነዉ። የመሰለንን ተናግረን እንድናሳምን ወይም እንድናምን ተደርገገን የተቀረጽን እንጂ አመራሮች የማይጥማቸዉ እንኳ ቢሆን እንኳንስ ሽጉጥ ሊመዘዝብን “...ከእንግዲህ ይህችን የማትፈለግ ሀሳብ ስትናገር እሰማህና ወዮልህ....” ተብለን አላደግንም። ሳልንሳቀቅና ሳንሸማቀቅ ለህዝብ ይጠቅማል ብለን የምናስበዉን የመናገር ድፍት እንዲኖረን ነገር ግን ድርጅታዊና ሀገራዊ ጥቅም ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ በዘፈቀደ ማዝረክረክ እንደሌለብን፣ለይተን ማወቅ እንድንችልና እንዲህ አይነት ጉዳዮች ሲያጋጥሙ የዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት ስርአትን ተከትለን ለበላይ አካላት ዉሳኔ ማቅረብ እንደሚኖርብን በአግባቡ የተማርን ነን። መብት ብቻ ሳይሆን ስነምግባርንና ግዴታዎችንም የተማርንበት ድርጅት ነዉ።ስለሆነም የህወሓት ልጆች በመሆናችን እድለኞች ነን። ይህ ጉዳይም የድርጅታችንም ሆነ የመንግስታችን ፖለቲካዊ ህይወት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ የሚከላከል እንጂ የሚፈታተን አይደለም። በመሆኑም በድርጅት ሳይሆን በግለሰብ ስም የተዘጋጀ ነዉ። ሀሳብን በነጻነትና

ባለመሸማቀቅ መግለጽን በተመለከተ ከዚህ ጽሁፍ መጀመር ጋር ተያይዞ ያገጠሙ የአስተሳሰብ ግጭቶች ብዙ ናቸዉ። ከሰላም ጽንሰሀሳብ ጋር የተያያዘዉን እንጠቁም። የመኖር ወይም ያለመኖር ምርጫን የማያስከትል ካልሆነ በስተቀር የሰላም ጉዳይ የህወሓቶች/ኢህአዴጎች እንደዚሁም የኢፌዴሪ መንግስት የህይወት መመሪያ ነዉ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ሰላምን ለማስፈን ሲባል በፖለቲካዊ አስተሳሰብ ጭቅጭቅ የግድ ሊሆን ይችላል ። "ግንባር ወይስ አሃዳዊ ፓርቲ" የተሰኘዉ ይህ ጽሁፍ ያልጣማቸዉ ግለሰቦች አልጠፉም። አለመጣም ብቻ ሳይሆን ማሸማቀቅ አዝማሚያ ተስተዉሎባቸዋል። ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ መረማመድ ይሏል እንዲህ ነዉ።

## *በአመክንዮ መርታት እንደማይሆንላቸዉ ሲያዉቁ የቀይሽብር ስርአት አስተሳሰብ ሰለባዎች "ሽብርተኛ" በሚል ቅፅል ስም ያሸማቅቁኝ ጀመር*

እነዚህ በአደገኛ አሰላለፍ እየተጓዙ ያሉት ግለሰቦች ሰላም እንፈልጋለን በሚል ሰበብ የዚህን ጽሁፍ አሰተሳሰብ አራማጆች ምክንያት "ሽብርተኛ" የሚል ቅጽል ስም ሰጥተዉላቸዋል። እቅጩን እንነጋገር ከተባለ ሽብርተኞቹ በድብቅ ጉዞ እየተጓዙ ያሉት እነዚህ አካላት ናቸዉ። ሽብርተኝነት የሚገልጸዉ አሁን ያለዉን የኢህአዴግ አወቃቀር በመጠምዘዝና ከብሄር ብሄረሰቦች ይሁንታ ዉጭ አሃዳዊ የፖለቲካ ድርጅት በመመስረት ዛሬ የተቀዳጀነዉን ሀሳብን የመግለጽ ነጻነትን ለመደፍጠጥ እያሸበሩን ያሉትን እንዚህን አደገኛ ተጓዦች እንጂ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ የተጎናጸፍነዉ ሰላም እንዳይደፈርስ ህጋዊ የፖለቲካ ትግል የምናደርገዉን የቁርጥ ቀን የህወሓት/ኢህአዴግ ልጆችን አይደለም። እነዚህ አካላት በእርግጥም ሊረቱ የሚችሉበት ህገመንግስታዊ እና ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ካላቸዉ በሰለጠነ መንገድ ሀሳባቸዉን የማቅረብ መብት

አላቸዉ። ይህን ማድረግ ተስኗቸዉ የግለሰቦችን ፖለቲካዊ እምነትና አመክንዮ በማስፈራራትና በማሸማቀቅ ለብሄር ብሄረሰቦች እዉቅና እናዳይበቃ መታገል ግን ከማደናገሪያነት ያለፈ ትርጉምም ዉጤትም አይኖዉም። ዛሬ ሀሳባችንን የመግለጽ ነጻነታችንን እንዳንጠቀም "ሽብርተኛ" የሚል ስም ከሰጡን ነገ ስልጣን ቢይዙና የኢህአዴግን ህልዉና ቢያጠፉ አንድ ቃል ተነፈስን ቁጥር እንደሚያጠፉን ይታመናል። እንዚህ አካላት በተጨባጭ የሽብር ተግባር ዉስጥ ተሰልፈዉ ለፍርድ የበቁት የተቃዋሚ እና የዉጭ ሀይሎች አጋሮች እና አስተሳሰብ ተሸካሚዎች ስለመሆናቸዉ ጥርጥር የለንም። ለእስር የበቁት ለብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች እኩልነት እና ነጻነት የቆመዉን የኢህአዴግ ስርአትና አስተሳሰቡን በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በሚፈጸም የሽብር ተግባር

## የምርጫ 97ን አደገኛ አመጣጥ በዉኑ ያጤነ በዚህች አገር የፖለቲካ ትግል ዉስጥ ተኝቶ አያድርም!

ለማስወገድ እና ለማኮላሸት በመሰለፋቸዉ ነዉ።የብሄር ብሄረሰቦች የትግል ዉጤት የሆነዉን የኢህአዴግ አወቃቀር ለማስቀጠል የምናራምደዉን አስተሳሰብ ለማኮላሸት የሚተጉትም የእነዚህ አካላት አስፈፃሚዎችና አጋሮች እንደሆኑ ይሰማናል። ዛሬ ሽብርተኛ የሚል ስም ካወጡልን አይሳካላችዉም እንጂ ተሳክቶላቸዉ ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማፍረስ አሀዳዊ የፖለቲካ ድርጅት የመሰረቱ እለት አንዲት ቃል ስንተነፍስ እንደቀድሞዉ ዘመናቸዉ በቀይ ሽብር ወይም ለብሄሮች ማንነትና ህልዉና የቆመ ሽብርተኛ በሚል ዘመቻ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ሊረሽኑን እንደሚችሉ ቅንጣት ታህል አንጠራጠርም። ያኔ ደግሞ እጅና እግሩን አጣምሮ የሚያይ አይኖርም። ለመብቱ የሚታገል ህዝብ ነፍጥ ያነሳል። ዛሬ ላይ ሆነን ፖለቲካዊ ጭቅጭቁን የፈለግንበት መሰረታዊ ምክንያትም ይኸዉ ነዉ። ነፍጥ

ለማንሳት የሚያስገድድ ድርጅታዊ ሰብእና ከመከሰቱ በፊት ዛሬ ላይ ተጨቃጭቀን የአሃዳዊ ፓርቲነት አስተሳሰብን ግብአተመሬት ማስገባት ይኖርብናል።ለዚህም የወረስነዉ ሀላፊነት አለብን። ዓላማችን ዛሬ ተጨቃጭቀን የነገዉ ሰላማችንን ማስጠበቅ ነዉ። ስለዚህ ካረጀ ካፈጀዉ የሽብር እና የፖለቲካ ተግባራቸዉ መታረም ያለባቸዉ እንርሱዉ እንጂ የእኛ አስተሳሰብ አይደለም! የምርጫ 97ን አደገኛ አመጣጥ በዉኑ ያጤነ በዚህች አገር የፖለቲካ ትግል ዉስጥ ተኝቶ አያድርም!

*ይህ አቋማችን የሚያሳጣን ምንም አይነት ጉዳይ ቢኖር እንኳ የእምነት ጉዳይ ነዉና የሚሆነዉን ሁሉ በጸጋ እንቀበላለን። ጉዳዩ ህወሓትንና ለህወሓት ዓላማ የወደቁትን የመምረጥና ያለመምረጥ በመሁኑ በጽናት የምንታገልለት ነዉ። ቢሆንም ግን ጉዳዩ የብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች እምነትና ጉዳይ በመሆኑ 99. 9 % ያህሉ ድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች እንደሚደግፉት ቅንጣት ታህል አንጠራጠርም።*

*ህወሓት/ኢህአዴግ ደግሞ ከወከሉት ብሄር*

# ብሀርሰቦችና ህዝቦች እምነት ዉጭ ምንም ማድረግ አይችልም።

ለዚህ ጽሁፍ ምክንያት በሆነን መሰረታዊ የመርህ ጉዳይ ላይ ያለምንም መሸማቀቅ ሀሳባችንን ገልጸንበታል እንገልጽበትማለን። ስለሆነም በደርግ ዘመን እንኳንም በአደባባይ ለመናገር የሚያስችል እድሜ ላይ አልደረስን። ያኔ ቢሆን ኖሮ ይዘነዉ በቀረብነዉ በዚህ ጉዳይ ላይ በግልጽ ልንከራከርበት ይቅርና በህይወት እንድንቆይም ባልተፈቀደልን ነበር። የዘነዉ የቀረብነዉ ጉዳይ የብሄር ብሄረሰቦች የወደፊት እጣ ፈንታ እና ሁለንተናዊ መብቶች ተሟልቶ የመከበርንና ያለመከበርን የሚፈታተን ነዉ። ስለሆነም  አስተሳሰቡ በእንጭጩ እንዲቀጭ  ያሉንን የፖለቲካና የህግ አመክንዮዎች ክብር በተሞላበት ሁኔታ እናቀርባለን። ያመነበት  ሀሳባችንን ያዳብረዋል።ስለብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብቶች በአስተማማኝ ሁኔታ መከበር ሲል ይታገልለታል። ያላመነበት ተቃራኒ  ሀሳቡን ያቀርብበታል። ይህንንም ባህል ያዳበርነዉ ከድርግ ሳይሆን  ከነጻነት አባታችን  ከህወሓት/ኢህአዴግ ነዉ። ስለሆነም ለህወሓት ህልዉና በተጠንቀቅ እንቆማለን። ጉዳዩ ኢህአዴግ ግንባር ይሁን ወይስ አሃዳዊ ፓርቲ? ለምን? በሚለዉ መሰረተ ሀሳብ ላይ የሚያጠነጥን ነዉ።

በዚህ ጉዳይ ላይ የበኩላችንን ሀሳብ ለማቅረብ ስንወስን የቀድሞዉ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በትግል ወቅት ስላጋጠመ ሁኔታ የተናገሩት ሀሳብ ዉስጣችን እየተመላለሰ ነዉ። ለዚህም ነዉ ለብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና በጽናት እንቆማለን የምንለዉ። እንዲህ ብለዉ ነበር!

*“.....አንድ ድርጅት ህይወቱን ከገበረ በኋላ .... ጭራቅ ሆኖ ያንን ግለሰብ ሊዉጥ ወይም የዚያን ግለሰብ ተስፋ ሊያጨልም የሚችልበት ሁኔታ ሲፈጠር የሚኖረዉ ሁኔታ..... ከሞት የባሰ ነዉ። .....የታገሉለት ድርጅት ጭራቅ ሆኖ ዓላማቸዉን ሲዉጥ...፣ ጉም ሆኖ ሲበን፣ሲተን እና መሃል ሜዳ ላይ ተበትነዉ ሲቀሩ ....በጣም አስከፊ ሁኔታ ነዉ....” መለስ ዜናዊ*

*በበኩላችንም ኢህአዴግ የነውጠኛዉ ቅንጅት እጣ ፈንታ እንዲገጥመዉ አንሻም። የብሄራዊ ድርጅቶች የትግል ዓላማና ስኬት በሚፈጠረዉ አሃዳዊ ፓርቲ ዉስጥ እንደእስስት እየተጓዙ በሚደራጁ ጭራቆች እንዲበላ ስለማንሻ የዉስጥም የዉጭም አፍራሽ ሀይሎች ቢኖሩ አምርረን እንታገላቸዋለን!*

*“ይህ ክፉና የህልዉናዬ አደጋ የሆነዉ የአደረጃጀት ሃሳብ ከላዬ ላይ ካልተነሳ አልወርድም!”*

የካቲት 10 ቀን ምሽት 2008 ዓ.ም. በእዉን በተከሰተ አጋጣሚ ላይ የተመሰረተ ተምሳሌታዊ ሀሳባችንን እናስከትል ። በምንሰራበት መሲሪያ ቤት ነዉ። የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነት ተምሳሌት የሆነዉ የኢፌዴሪ ሰንደቅዓላማችን ይህ ጽሁፍ ተጀምሮ በቀጠለበት ቀንና በማግስቱ (የካቲት 10 እና 11 ቀን 2008 ዓ.ም. )አልወርድም ብሎ ታይቷል።ሰንደቅዓላማችን። የመከራከሪያ ሀሳባችንን ለመደገፍ ሰላማዊ የተቃዉሞ መልእክት እያስተላለፈ እንደሆነ ተሰምቶናል-በወቅቱ። የክልሎችም ሰንደቅዓላማዎች ለህልዉናቸዉ ሲሉ በተመሳሳይ አቋም እንደሚዉለበለቡ ተስፋ አደረግን-በወቅቱ። በምንሰራበት መስሪያ ቤት የተሰቀለዉ ሰንደቅዓላማችን አጠገቡ ካለዉ ሌላ የሰንደቅዓላማ መስቀያ ብረት ጋር በአንደኛዉ ጫፉ ተያይዟል። በዚህም ምክንያት በሁለቱም ጫፎቹ ወደጎን ተወጥሮ አርማዉ በሁለቱም ብረቶች መሃል ላይ ሆኖ እንደተወጠረ ሲዉለበለብ ተስተዉሏል። በመሆኑም ሰንደቅዓላማዉን በሰዓቱ ማዉረድ አልተቻለም። ሙከራዉ ስላልተሳካ

አንቃሮ ከመመልከት ባለፈ ምንም ማድረግ አልተቻለም ። የካቲት 10 ቀን። የሰንደቅ ዓላማዉ አርማ "እኔ ከሌለሁ የተረጋገጠዉ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ጉዳይ አደጋ ላይ ሊወድቅ ስለሚችል አልወርድም" ያለ ይመስላል። በሁለቱም ብረቶች መሃል ቤት ተወጥሮ የመታየቱ ጉዳይ "የማን ነኝ? የብሄራዊ ፖለቲካ ድርጅቶችን ህለዉና አስከብሮ ከሚቀጥለዉ የኢህአዴግ ግንባር ወይስ ለእኔም ሆነ ለብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና መጥፋት ምቹ ሁኔታዎችን ለሚያመቻቹ ጥቂት የኢህአዴግ አሃዳዊ ፓርቲነት አስተሳሰብ አራማጆች ነኝ?" የሚል አቤቱታ የሚያሰማ ይመስል ነበር። መሃል ቤት የተወጠረዉ የሰንደቅዓላማችን አርማ! "…ኢህአዴግ ከብሄራዊ ድርጅቶች ግንባርነት ወደአሀዳዊ ፓርቲነት የሚሸጋገር ከሆነ ለብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና እዉቅና ህገመንግስታዊ ድጋፍ የተሰጠኝን እኔን አርማዉንም ለማስወገድ የተዘጋጁ ጥቂት ሀይሎች በይፋም ባይሆን በድብቅ ማሰብ የጀመሩ ስለመሰለኝ እምቢኝ አሻፈረኝ፤ ይህ ክፉ ሀሳብ ከላዬ ላይ ካልተነሳልኝ አልወርድም…" ያለ  ይመስል ነብር። በበኩላችንም "ይህ ሰንደቅዓላችን ስጋታችን ገብቶት ይሆን እንዴ፤ሰምቶን ይሆን እንዴ?" ማለታችን አልቀረም። ለማንኛዉም ሰንደቃላማችንም "ይህ ክፉና የህልዉናዬ አደጋ የሆነዉ የአደረጃጀት ሃሳብ ከላዬ ላይ ካልተነሳ አልወርድም!" በሚል መፈክር የደገፈን ያህል ተሰምቶናል። የአርማዉን ህገመንግስታዊ ትርጉም እና የኢህአዴግ በግንባርነት መቀጠልን  ህጋዊና ፖለቲካዊ ተዛምዶ ለማሳየት መሞከራችን አይቀርም። ብራቮ ሰንደቅዓላማችን! "ግንባር ወይስ አሃዳዊ ፓርቲ? ለምን?"

## *የሰንደቅዓላማችን አርማ  ህገመንግስታዊ ትርጉም እና የኢህአዴግ ግንባርነት ፖለቲካዊ ተዛምዶ*

የአሁኑ የኢህአዴግ ድርጅታዊ ቅርጽና ሰብእና እና የኢፌዴሪ ህገመንግስት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸዉ። በኛ እምነት ኢህአዴግ የቆመባቸዉ የብሄራዊ ድርጅቶች የማእዘን ድንጋዮች(ምሰሶዎች) ከተነቀሉ ወይም ህልዉና ካጡ የህገመንግስቱን መሰረታዊ ምሰሶዎች /ድንጋጌዎች/ ለመናድ ምቹ ሁኔታ ተፈጠረ ማለት ነዉ። ኢህአዴግ በዚህች አገር ዉስጥ ያሉት የፖለቲካ ድርጅቶች የብሄር ብሄረሰቦችን ሁለንተናዊ እኩልነት ያረጋገጠዉን ህገመንግስት አክብረዉ ነገር ግን የኢህአዴግ አማራጭ ፓርቲዎች ሆነዉ እንዲቀርቡ የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን ተከትሎ የድርሻዉን እየተወጣ ነዉ። የአዉራ ፓርቲነት ሚና ለመጫወት ሲያቅድም ህገመንግስቱን ለመናድ ቅርብ የሆኑ የፖለቲካ አደረጃጀቶችና አስተሳሰቦችን እያበረታታ ለመሄድ ሳይሆን የልማታዊ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን፣የኢፌዴሪ ህገመንግስትን እና አሁን ያለዉን ስርአተመንግስት የፈጠሩት የፖለቲካ ርእዮተዓለሞች እንደዚሁም መስዋእትነት የተከፈለባቸዉን የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጉዳዮች ሳይሸራረፉ ማስቀጠል የሚችሉ ፓርቲዎችን ከመደገፍ ጋር ተያይዞ የሚታይ ነዉ። ይህን እንደ እንደ የፖለቲካ ስልት አቅዶ መንቀሳቀሱ ደግሞ ከፖለቲካ አንፃር ተፈጥሮአዊ ነዉ። በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ሉኣላዊ ስልጣን ላይ የተመሰተ ህገምንግስት እና ስርአተ መንግስት ማየት አልፈልግም የሚሉ ጽንፈኛ ፖለቲከኞች ያለምንም ከልካይ ለምርጫ በሚንቀሳቀሱበት አገር የእርሱን (ኢህአዴግ)ፈለግ የተከተሉ የፖለቲካ ድርጅቶች መኖር ላይ የተመሰረተ የአዉራ ፓርቲነት ሚና ለመጫወት በይፋ የመንቀሳቀሱ ጉዳይ የበለጠ ተመራጭ ያደርገዉ እንደሆነ እንጂ ሊያስተቸዉ አይችልም። ማንነታችንን ለማጥፋት የሚደነፉት የከተማ ላይ አርበኞች መብት ኖሯቸዉ በሚንቀሳቀሱበት አገር በአዉራ ፓርቲነት ሚና ልማታዊ ድሞክራሲያዊ እና የኢፌዴሪ ህገምንግስ አስተሳሰቦችን

የሚያራምዱ ድርጅቶች ልእልና እንዲኖራቸዉ በዓላማ ደረጃ ቢንቀሳቀስበት ፖለቲካዊ ስልትና መብት እንጂ ሀጢያት ሊሆን አይችልም።

በኢህአዴግና በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል እስከአሁን ያለዉ ልዩነትም ህገመንግስትን ጨምሮ ያለዉን እያጠናከሩ በመሄድ የፖዘቲቭ ድምር ዉጤትና የነበረዉን አፈራርሶ ከዜሮ በመጀመር ላይ የተመሰረተ የዜሮ ድምር ዉጤት ጨዋታ ነዉ። ኢህአዴግ እስከዛሬ ድረስ በስልጣን የቆየበትና በዚህ ፖለቲካዊ መርሆ እስከቀጠለ ድረስ በአሸናፊነት ሊዘልቅ የሚችልበት ምስጢርም ይኸዉ ነዉ። ኢህአዴግ የመሰረት ድንጋዮቹን ህልዉና አጥፍቶ ወደአሃዳዊ ፓርቲነት ከተቀየረ ግን ተቃዋሚዎች የእኩልነትና የተከባብሮ መኖር መሰረት የሆነዉን ህገመንግስታችንን አክብረዉ እንዲንቀሳቀሱ ሲተቹበት የነበረዉና ዉጤት ያላመጡበት አስተሳሰብ የበላይነቱን ይጎናጸፋል። ምክንያቱም ኢህአዴግ አሃዳዊ ፓርቲ ከሆነ በራሱ ጊዜ ወደተቃዋሚዎች ጎራ ለመቀላቀል የሚያስችል በር ከፈተ ማለት ነዉ። በልማታዊና አብዮታዊ ዲሞክራሲ አስተሳሰብ የአዉራ ፓርቲነት ሚናዉን ወደማይወጣበት ደረጃ ላይ መድረሱ አይቀርም። ተቃዋሚዎች በኢትዮጵያ ዉስጥ የአፍርሶ መገንባት አገዛዝ ስርአትን ለማስፈን ሲተጉበት ለቆዩት የቀዉስ መርሆ ተግባራዊነት በሩን ክፍት እንዳደረገ ይቆጠራል። ተቃዋሚዎች ስልጣን በያዙ ማግስት አሁን ያለዉን የኢፌዴሪ ሰንደቅዓላማ እንደሚያሻሽሉት ደጋግመዉ ሲነግሩን ቆይተዋል። ዋነኛዉ ጠባቸዉ ደግሞ ከአርማዉና ከወከለዉ ፖለቲካዊና መብታዊ ትርጉም ጋር ነዉ። አርማዉ የብሄር ብሄረሰቦች፣የህዝቦችና የሀይማኖቶች እኩልነትንና ተፈቃቅዶ የመኖር ተምሳሌት እና ተልእኮ እንጂ ሌላ ክፉ ሃሳብ የለዉም። ይህን በጎ ተልእኮ የማደብዘዝ ወይም የማጥፋት ዓላማ ያለዉ ማንኛዉም አካል ደግሞ በኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ዘንድ ከእንግዲህ ተቀባይነት

የለዉም። የኢህአዴግ የትግል ዓላማና አፈጣጠርም ከዚህ ዓርማ ትርጋሜ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸዉ። ከኢፌዴሪ የሰነደቅዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001 ክፍል ሶስት ዉስጥ ከዚህ ጉዳይ ጋር ቀጥታ ተዛማጅነት ያላቸዉን ድንጋጌዎች በቅድሚያ እንመልከት። የአዋጁ አንቀፅ 5 የሰንደቃላማዉን ምንነት አስመልክቶ "…..የህዝቦች በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት መግለጫ…." መሆኑን ሲደነግግ በተመሳሳይ ሁኔታ ስለሰንደቅዓላማዉ አርማ የሚያስረዳዉ አንቀጽ 8 ንኡስ አንቀጽ 2፣3 እና 4 በቅደም ተከተል፡-

- "ቀጥታና እኩል የሆኑት መስመሮች የብሄሮች፣የብሄረሰቦችና የህዝቦች እንዲሁም የሀይማኖትን እኩልነት ያመለክታል"
- "ቀጥታና እኩል ከሆኑት መስመሮች የተዋቀረዉ ኮከብ የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ብሄረሰቦችና ህዝቦች በመፈቃቀድ የመሰረቱትን አንድነት ያመለክታል"
- "ቢጫ ጨረር በመፈቃቀድ አንድነት ለመሰረቱት ብሄር ብሄረሰቦች የፈነጠቀዉን ብሩህ ተስፋ ይጠቁማል"

የሚሉ ድንጋጌዎችን ይዟል። ከዚህ አኳያ ኢህአዴግ ሲጀመር በብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና ላይ ተመስርቶ ከተዋቀረባቸዉ ዋነኛ ምክንያቶች ዉስጥ፡-

- ብሄራዊ ድርጅቶች የክልሎችና የብሄር ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትና ህልዉና ተምሳሌት ናቸዉ። ክልሎች በዉስጣቸዉ ያቀፏቸዉ ብሄሮችና ብሄረሰቦች እዉቅና ተጠብቆ የሚኖርባቸዉም ናቸዉ። ብሄራዊ ድርጅቶች ለፌዴራልና ለክልል ምክርቤቶች ዉክልና ሲወዳደሩ በየክልሉ ያሉትን ብሄሮችና ብሄረሰቦች በአግባቡ በመወከል ነዉ። አሁን ያለዉ የኢህአዴግ እና የተቃዋሚዎች ተፈጥሮ እንደዚሁም በህገመንግስቱ ላይ ያላቸዉ መሰረታዊ ልዩነት በዚህ

ይገለጻል። ለፌዴራል እና ለየክልሉ ያለዉ የክልሎች ዉክልና ጉዳይ ኢህአዴግ ከአዲስ አበባ እና ከድሬዳዋ ለፌዴራል እንደዚሁም ለአዲስ አበባና ለድሬዳዋ ምክር ቤቶች ከሚያደርገዉ የዉክልና ዉድድር የተለየ ነዉ። የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ተጠሪነት ለፌዴራል መንግስት በመሆኑ እና በአንድ ክልል በተሰየመ የብሄር ብሄረሰብ አስተዳደር ባለመዋቀራቸዉ የኢህአዴግ እጩዎች በቀጥታ ህወሓትን፣ኦህዴድን፣ደኢህዴንን ወይም ብአዴንን እና እነርሱ የወከሏቸዉን ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በመወከል አይወዳደሩም። ኢህአዴግ በየክልሉ ሲወዳደር ግን የሚቀርቡት እጩዎች የክልሉን ብሄር ብሄረሰብ የሚወክሉት የብሄራዊ ድርጅቱ አባላት ናቸዉ። ኢህአዴግን የመሰረቱት የእነዚህ ብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና ከጠፋ ግን ብሄር ብሄረሰቦች በአግባቡ የሚወከሉበት መሰረቱ ይናዳል። ብሄራዊ ድርጅቶቹ ከሌሉ በዚያ ክልል የሚኖረዉ የዉክልና ዉድድር ልክ እንደ አዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ አሃዳዊ የፖለቲካ ድርጅትን በሚወክሉ የአንድ ድርጅት አባላት ላይ እንዲመሰረት ሊያስገድድ ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ የብሄር ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መሰረታዊ መብት በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ተግባራዊ አይሆንም። የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ጽንሰሀሳብ የብሄር ብሄረሰቡን ቋንቋ ለስራ፣ለትምህርት፣ለፍትህና ለዳኝነት ተግባራት፤ የብሄር ብሄረሰቡን ባህልና ወግ የመጠቀምና የማሳደግ መብት፤ ከብሄር ብሄረሰቡ በወጡ ተወካዮችና አስተዳዳሪዎች የመተዳደር መብት፤የክልሉን ሀብት የመጠቀምና የማስተዳደር መብት ወዘተ ያጠቃልላል። ኢህአዴግ አሃዳዊ የፖለቲካ ድርጅት ከሆነ ግን ሁለት ፍላጎቶች መፋጠጣቸዉ አይቀርም። አንደኛዉ ፍላጎት የብሄር ብሄረሰቦች ደም ፈሶበትና አጥንት ተከስክሶበት ተግባራዊ በሆነዉ

ህገመንግስት መሰረት በተዋቀሩት ክልሎች አማካኝነት የብሄር በሄረሰቦችን ሁለንተናዊ መብትና እኩልነት እያረጋገጡ ያሉት የአከላለልና የዉክልና ስርአቶች ተጠብቀዉ እንዲቀጥሉ

## *ታሪካዊ ሃላፊነት አለብን*

የሚታገል ነዉ። ሌላኛዉና መጤ ፍላጎት ደግሞ ኢህአዴግ አሃዳዊ የፖለቲካ ድርጅት እስከሆነ ድረስ የክልሎች አስተዳደርም ሆነ የዉክልና ስርአት ልክ እንደአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ብሄራዊ ዉክልናን እና ህልዉናን ገሸሽ የሚያደርግ ነዉ። ለክልሎች የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብት የሚያጎናጽፈዉን ክልላዊ የአስተዳደር ስርአት ለማጥፋት የሚተጋ ይሆናል። ማለትም የኢህአዴግ አባላት ባልተወለዱበት ክልልና አካባቢ እንደዚሁም በትዉልድ ለማይወክሉት ብሄር ብሄረሰብ የመወዳደር መብታቸዉ የተጠበቀ ይሆናል። ይህ መብታቸዉ እስከተጠበቀ ድረስ ደግሞ ለምሳሌ በሚወዳደሩባቸዉ ክልልሎች (የየትኛዉም ብሄር የሆነ አባል የምርጫ ህጉን መስፈርት እስካሟላ ድረስ በሁሉም ክልሎች የመወዳደር መብት ይኖረዋል) የኢህአዴግ አባላትን በጋራ የሚያግባባ የስራ ቋንቋ ያስፈልጋቸዋል። አሃዳዊ ፓርቲ እስከሆነ ድረስ አባላቱ በሁሉም አካባቢ አንድ የጋራ ቋንቋ እንዲኖራቸዉ የመጠየቅ መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ።

*በአሁኑ ጊዜ በክልልም ሆነ ከክልል በታች ያሉት የአስተዳደር መዋቅሮች የሚጠቀሙባቸዉ የአካባቢዉ ተወላጆች ቋንቋዎች ሁሉ ለአሃዳዊዉ የኢህአዴግ አባላት መብትና አመቺነት ሲባል በአንድ ቋንቋ የመተዳደራቸዉና የመዳኘታቸዉ ጉዳይ አስገዳጅ እየሆነ*

*ይመጣል። ወላይትኛ፣ስልጢኛ፣ጉራጊኛ፣ ከምባትኛ፣ሃድይኛ፣ሲዳምኛ ፣ሶማሊኛ ወዘተ ከዞን እስከ ቀበሌ ድረስ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ቦታ አይኖራቸዉም። በአማርኛ ወይም በሌላ ቋንቋ የመተካታቸዉ ጉዳይ አይቀሬ ይሆናል።*

ልክ በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ተግባራዊ እንደሆነዉ ይህ ቋንቋ በክልሎችም ተግባራዊ ሊሆን እንደሚገባዊ በፖለቲካ አደረጃጀትም ሆነ በህግ አስተሳሰብ አሳማኝ የሆኑ አመክንዮዎች መቅረባቸዉ አይቀርም። ይህም አሁን ካለዉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ቅራኔ ዉስጥ መግባቱ የግድ ነዉ።*ይህ ደግሞ በርካታ የመብት ጥሰትና በአስባቡም የተቃዎሞ ሰበቦችንና ግጭቶችን ማስከተሉ አይቀርም።*

- በዚህ መነሻነት አሁን ያለዉ የኢ.ህአዴግ ድርጅታዊ አወቃቀርና ተልእኮ የአንቀፅ 8 አስተሳሰን ለመተግበር የወሰነ ነዉ።እኩል እዉቅና እና ስልጣን ያላቸዉ ኢ.ህአዴግን የመሰረቱት ብሂራዊ ድርጅቶች ህልዉና ....ለብሂሮች፣ብሂረሰቦችና ህዝቦች... እኩልነት በተሰየሙት በሰንደቅዓላማዉ ቀጥታና እኩል መስመሮች ህልዉና የሚመሰል ነዉ።

*የሰንደቅ ዓላማዉ አርማ የኢ.ትዮጵያ ብሂሮች፣ብሂረሰቦችና ህዝቦች በመፈቃቀድ የመሰረቱትን አንድነት እንደሚያመለክተዉ ሁሉ ብሂራዊ ድርጅቶችም በዚሁ እምነትና አስተሳሰብ ኢ.ህአዴግን በግንባርነት የመሰረቱት ነዉ።*

የአጼዉና የደርግ ዘመን አቀንቃኝ ተቃዋሚ ድርጅቶች ይህን አርማ ለማጥፋት እንደሚፎክሩት ሁሉ በኢ.ህአዴግ አስተዳደር ዘመን ይህን አርማ ማጥፋት ማለት በብሂር ብሂረሰቦች እና ህዝቦች ህልዉና ላይ ብቻ የተመሰረተ አንድነት ለማስጠበቅ ይዞት የቀረበዉን ተልእኮ ማጥፋት ነዉ። በተነጻጻሪም የብሂራዊ ድርጅቶችን ህልዉና ያጠፋ በአሃዳዊነት ላይ

የተመሰረተ አዲስ ኢህአዴግ መፍጠር የአርማዉን ዓላማና ተልእኮ ለማጥፋት በርን ወለል አድርጎ እንደመከፈት ይቆጠራል።

*ብሄር ብሄረሰቦች ተፈቃቅደዉ በመሰረቱት አንድነት ምክንያት የፈነጠቀዉን ብሩህ ተስፋ ጨለማ እንደማልበስ ይቆጠራል።*

ሌሎች አሃዳዊ አወቃቀር ያላቸዉ የፖለቲካ ድርጅቶች በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ተቀባይነት ይኖረናል ብለዉ እስካመኑ ድረስ አርማዉን በማጥፋት ላይ ያለመ ህገመንግስታዊ ይዘት ይቅርና እንደቀድሞአቸዉ "በኢትዮጵያ ዉስጥ ኦሮሞ፤ትግራይ፣ሶማሌ፣ ወላይታ፣ጉራጌ ወዘተ የሚባል ብሄረሰብ የለም …" የሚል ፖለቲካዊ አጀንዳ ይዘዉ መቅረብ ይችላሉ። ህገመንግስት ለግጭትና ለሁከት እንደዚሁም በህግ ለተከለከሉ ሌሎች የወንጀል ተግባራት የማያነሳሳ እስካልሆነ ድረስ ሀሳብ ማቅረብን ይፈቅዳል። ብሄር ብሄረሰቦች ደግሞ ሀሳቡ ዘላቂ ሰላምና ልማት የሚያመጣላቸዉ ወይም የሚያርቅባቸዉ መሆኑን ገምግመዉ ይወስናሉ። ለግጭትና ለብጥብጥ ምክንያት እስካልሆነ ድረስ ሀሳብን ማራመድ አይከለከልም። ነገር ግን ያለ ብሄር፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ይሁንታ ስልጣን መያዝ የተከለከለ ነዉ። ምክንያቱም የሉአላዊ ስልጣን ባለቤቶች ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ናቸዉ። ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ላለፉት 20 እና ከዚያ በላይ ዕመታት ስልጣን መያዝ ያልቻሉበት ምክንያትም ይዘዉ የቀረቧቸዉ ሀሳቦች በሉአላዊ የስልጣን ባለቤቶች ይሁንታ በማጣታቸዉና ቦታ የሌላቸዉ በመሆናቸዉ ነዉ። አንዳንድ ጊዜ ተቃዋሚዎች ከ90 ሚሊየን ህዝብ ዉስጥ ከ2.5% በማይሞላ እንደአዲስ አበባ ባሉ ከተሞች እየተሹለኮሎኩ ይዘዉ በሚያቀርቡት ተቀባይነት የሌለዉ ሀሳብ ግርግር ሲፈጥሩ በአገር ደረጃ ትልቅ ተቀባይነት እንዳገኙ የምንቆጥር አንጠፋ ይሆናል።ያዉም ከዚህ ህዝብ ዉስጥ ሊደግፉቸዉ የሚችለዉ ያለፉት ስርአቶች ተጠቃሚ የነበረዉና ገፈት ቀማሽ ያልነበረዉ ቢጤአቸዉ የሆነዉ ጥቂት የህብረተሰብ ክፍል ነዉ።

ይህም በምርጫ ዉጤቶች ተደጋግሞ ሲወድቅ ቆይቷል። ይሁን ቢባልም እንኳ አዲስ አበባ ያለዉ ከ2.5 % የማይበልጥ ህዝብ (ያዉም በህግ የመወሰን መብት ያልተሰጠዉን ጨምሮ) ፍላጎት በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠረዉን በየክልሉ የሚገኘዉን የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት የሆነዉን ብሄር ብሄረሰብና ህዝብ ፍላጎት ሊወክል አይችልም። ስለሆነም የብሄራዊ ድርጅቶችን ህልዉና ደብዛ ያጠፋ አሀዳዊ ኢህአዴግ በአንቀጽ 8 ከተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተልእኮ አንፃር ሲመዘን ብዙዎች የወደቁለትን ዓላማ ለማፈራረስ ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥር በራሳቸዉ በብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች መዉደቁ አይቀርም። መምቻ ዱላዉን ቆርጦ እንደማቀበል ይቆጠራል። ኢህአዴግ ከግንባርነት ወደአሀዳዊ ፖለቲካ ድርጅትነት ቢሸጋገር ህገመንግስቱ የሚሸራረፍባቸዉን መሰረታዊ የመብት ጉዳዮች እያስመዘገብን ነዉ። አንድ በሉ።

- ጉዳዩን ከኢፌዴሪ ህገምንግስት አንቀጽ 5 ንኡስ አንቀፅ 3 ተልእኮ አንጻር እንመልከተዉ። ይህ አንቀጽ "….የፌዴሬሽኑ አባሎች የራሳቸዉን የስራ ቋንቋ በህግ ይወስናሉ….." የሚል ድንጋጌ አስፍሯል። ሲጀመር ኢህአዴግ የብሄራዊ ድርጅቶችን ህልዉና ካጠፋ የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦችን የራስን እድል በራስ ለመወሰን ስልጣን የሚሰጥ የአከላል ስርአት እንዳይኖር ተዘጋጅቷል ማለት ነዉ። ይህም የአሃዳዊ ድርጅቱ አባላት በሁሉም የመስተዳድር አካባቢዎች ያልምንን መስፈርት ሊወዳደሩና ሊያስተዳድሩ የሚችሉበት የአስተዳደር አወቃቀር ማስፈንን ግድ ይለዋል። ከዚህ ዉስጥ አንዱ የስራ ቋንቋ ነዉ። ስለሆነም አንድም በአሁኑ ጊዜ ያሉት የፌዴሬሽኑ አባሎች ለአሃዳዊዉ ኢህአዴግ በሚመጥኑ መልኩ እንደአዲስ መዋቀር ይኖርባቸዋል ሁለትም ብሄር ብሄረሰቦች እስከቀበሌ አስተዳደር መዋቅር ድረስ በመረጡት ቋንቋ የመተዳደር መብታቸዉን ለአሃዳዉዉ ኢህአዴግ ህልዉና እና ወጥ የሆነ አሰራር ሲባል መስዋእት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ስለዚህ አንቀጽ 5ም በራሱ በኢህአዴግ

ተፈጥሮ ምክንያት ተሰረዘ ማለት ነዉ። ሁለት በሉ።ልብ በሉ የብሄር ብሄረሰቦች የትግል ዉጤቶች አንድ በአንድ እየተሸራረፉ ነዉ። መሸራረፋቸዉ ደግሞ የመገንጠል መብት ጥያቄን ሊያስከትሉ ይችላሉ።

- ሌላዉ የማይታለፈዉ ድንጋጌ በአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀፅ 1 እና 3 በቅደም ተከተል የሰፈረዉ ነዉ። ድንጋጌዎቹ እንዲህ ይላሉ፦
    - "የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች የኢትዮጵያ ሉአላዊ ስጣን ባለቤቶች ናቸዉ"
    - "ሉአላዊነታቸዉም የሚገለፀዉ በዚህ ህገመንግስት መሰረት በሚመርጧቸዉ ተወካዮቻቸዉና በቀጥታ በሚያደርጉት ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል"

በድርጅታዊ አወቃቀሩ የብሄራዊ ፓርቲዎችን ህልዉና ያላረጋገጠ ወይም እዉቅና ያልሰጠ የፖለቲካ ድርጅት የብሄር ብሄረሰቦችን ሉአላዊ ስልጣን ባለቤትነት ሊያረጋግጥ አይችልም። ብሄር ብሄረሰቦች የሉአላዊ ስልጣን ባለቤት መሆን ካለባቸዉ እነርሱን በፌዴራልም ሆነ በክልል ደረጃ በቀጥታ የሚወክሉ ተመራጮች መኖር አለባቸዉ። በአንጻሩ ግን እነርሱን የሚወክሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ህልዉ እንዳይሆኑ ያደረገ የፖለቲካ ድርጅት በአንቀጽ 8 ንኡስ አንቀፅ 3 ስር ብሄር ብሄረሰቦች "…..በሚመርጧቸዉ ተወካዮቻቸዉ…." አማካኝነት እንዲወከሉ፤ዲሞክራሲያዊ መብታቸዉ እነዲረጋገጥ በዋናነት ደግሞ በዉክልናቸዉ ሉአላዊ የስልጣን ባለቤት እንዲሆኑ የማድረግ ተፈጥሮም ዓላማም አይኖረዉም። እንዲህ አይነት አሃዳዊ የፖለቲካ ድርጅት አባላቶቹን ለዉድድር የሚያቀርበዉ በብሄራዊ ዉክልና መስፈርት ሳይሆን በየትም ቦታ ወጥ በሆነ መንገድ(ልክ እንደአዲስ አበባና ድሬዳዋ) እንዲወዳደሩ በማድረግ ነዉ። አሁንም የብሄር ብሄረሰቦች መብቶች መሸራረፍ እንደቀጠሉ ነዉ።

የህገመንግስቱ የመሰረት ድንጋይ የሆኑት ድንጋጌዎችም እንደዚሁ ተቀናንሰዉ ወይም ተሻሽለዉ እያለቁ እንደሆነ አስተዉሉ። ሊከተል የሚችለዉንም አደጋ ግምት ዉስጥ አስገቡ። ሰበቡ ይህ ከሆነ አሃዳዊ ኢህአዴግ ተቀባይነት ይኖረዋል? አይመስለኝም! ለህዝብ ሳይበቃ በዉስጥ ግጭት መፈራረሱ አይቀርም። ዛሬ እንዲህ ፍርጥርጥ አድርገን እንድንነጋገርበት የምፈልግበት ምክንያትም ክፉ መንፈስና ዓላማ ስላለን አይደለም። ሊሆን የማይችለዉን ከወዲሁ አርቀን በማሰብ መዳን ያለበትን ማዳን ስላለብንና ይህም ድርጅታዊ ሀላፊነታችን በመሆኑ ነዉ። አባቱን ማወቅና ማዳን የማይፈልግ ካለ እርሱ ማንነቱን የማይፈልግ ነዉ። እኛ ደግሞ ማንነታችን ተጠብቆ እንዲኖር የምንታገል የህወሓት/ኢህአዴግ ልጆ ነን። ስለዚህ የአባታችንን እዉቅና ማስቀጠልና ማዳን ታሪካዊ ሀላፊነት አለብን።

- ኢህአዴግ አሃዳዊ ፓርቲ ከሆነ በህገመንግስታችን ላይ የሚከተለዉ መዘዝ እንደቀጠለ ነዉ። አንቀጽ 39ን እንመልከት። የብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦችን መብት ይመለከታል። በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1፣2 እና 3 በቅደም ተከተል፦

  "…ማንኛዉም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለዉ መብቱ በማንኛዉም [ሁኔታ] ያለገደብ የተጠበቀ ነዉ…"

  "….ማንኛዉም የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰብ ህዝብ በቋንቋዉ የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋዉን የማሳደግና ባህሉን የመግለፅ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለዉ…"

  "…ማንኛዉም የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ህዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለዉ…….በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ዉስጥ ሚዛናዊ ዉክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል" የሚሉ ድንጋጌዎች ሰፍረዋል።

## “አሳን ለማጥፋት ባህሩን ማድረቅ”

ከላይ የሰፈሩት የአንቀጽ 39 ድንጋጌዎች አሃዳዊ የፖለቲካ አወቃቀር ካለዉ ድርጅት ጋር የሚጋጩ ብቻ ሳይሆን በቀጥታ የሚላተሙ መሆናቸዉን ማስረዳት አይስፈልግም። እነዚህ ድንጋጌዎችና አሀዳዊ ተፈጥሮ ያላቸዉ የፖለቲካ ድርጅቶች ለየቅል ባይሆኑ ኖሮ ኢህአዴግን የሚቃወሙ የፖለቲካ ድርጅቶች ስልጣን በያዙ ማግስት እነዚህንና ሌሎች የህገመንግስቱ የመሰረት ድንጋይ የሆኑ ድንጋጌዎችን እንደሚያሻሽሉ የሚያስረዱ አማራጭ የፖለቲካ ፕሮግራሞችን ይዘዉ ባልቀረቡ ነበር። ብሄር ብሄረሰቦችም በመረጧቸዉ ነበር። ወደህገመንግስታዊ ትንታኔዉ ከማለፋችን በፊት በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የተከሰቱ ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮችን በምሳሌነት እናስታዉስ። ከዓመታት በፊት ነዉ። ወጋጎዳ የተሰኘ አዲስ ቋንቋ ተፈጠረ። በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት። “ወጋጎዳ” የወላይታ፣ የጋሞ፣ የጎፋ እና የዳዉሮ ብሄሮች መጠሪያ የመጀመሪያ ፊደል ተወስዶ በአህጽሮት የተፈጠረ የአርቴፊሻል ቋንቋ ስም ነዉ። መሰረታዊ ዓላማዉ የእነዚህን ብሄሮች የተናጠል ቋንቋ በማጥፋት በሌላ ቋንቋ በመተካት የጋራ ቋንቋ እንዲጠቀሙ ማስገድድ ነበር። በመሰረቱ አንድ ቋንቋ የአንድ ብሄር ሁለንተናዊ መግለጫም መገለጫም ነዉ። የብሄሩ ታሪክ፣ወግና ባህል፣ በአጠቃላይ ደግሞ ማንነቱ የሚገለጸዉም ሆነ የሚዳብረዉ፣ ተጠብቆ የሚኖረዉና ለትዉልድ የሚተላለፈዉ በቋንቋዉ ነዉ። የብሄሩ ቋንቋ እንዲጠፋ ከተደረገ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ “የብሄሩ ህልዉና እና ማንነት እንዳይኖር ተፈርዶበታል” ብሎ በድፍረት መናገር ይቻላል። የብሄሩ ማንነትና ተያያዥ ጉዳዮች በሌላ በተዉሶ ቋንቋ ሊገለጽ ይችላል የሚል መከራከሪያ ቢቀርብ እንደ ቆፍጣና አባታችን ከወደድሽኝ ከነምናምኔ የሚል መልእክት ለማስተላለፍ “ ሰብኣይን ፈቲኽን ጭሕሚን ጻሊእኽን….” በማለት

የሚሰነዝሩትን ቀልድ ያስታዉሰናል። ወይም ሰዉ በላዉ ደርግ ከመሬቱ እንጂ ከህዝቡ ፍላጎት  የለንም በሚል እኩይ አስተሳሰብ “አሳን ለማጥፋት ባህሩን ማድረቅ” በማለት ያከናወነዉን የጥፋት ዘመቻ እንድናስታዉስ ያስገድደናል። የትግራይ ህዝብ እና ወያኔ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች መሆናቸዉን የተገነዘበዉ ደርግ ወያኔን ለማጥፋት የወያኔ ምንጭ የሆነዉን የትግራይ ህዝብ የማጥፋት ስትራቴጂ ቀየሰ። በተመሳሳይ ሁኔታ ዘላቂነት ያለዉ የማንነት መገለጫና ማቆያ የሆነዉ የአንድ ብሄር ቋንቋ ከጠፋ በጊዜ ሂደት ብሄሩ በሌለ ብሄር መገለጫ ተዉጦ ደብዛዉ መጥፋቱ አይቀርም። በሌላ በኩል ደግሞ አንድን ብሄር ከወደድነዉና ህልዉናዉ እንዲቀጥል የምንታገልለት ከሆነ ለህልዉናዉ አይነተኛ መሳሪያ የሆነዉን ቋንቋዉንም መዉደድና መንከባከብ ይኖርብናል።

## “ወጋጎዳ”-እስከአሁን ሃዘን ላይ እንደማይሆኑ ተስፋ እናደርጋለን

የተከበሩት አባታችን  “ ሰብኣይን ፌቲኽን ጭሕምን ጸሊእኽን….” ሲሉ “……ባል ፈልገሽ ነገር ግን ጺም ጠልተሽ እንዴት ይሆናል ” ማለታቸዉ ነዉ። ስለሆነም የብሄሩን ህልዉና ከወደድን በቅድሚያ ለማንነቱና ለህልዉናዉ መጠሪያ የሆኑትን ያለማንገራገር( Out rightly) መዉደድ ይኖርብናል። ስለዚህ በሌላ በተዉሶ ቋንቋ ሊገለጽም ሊጠቀምም ይችላል የሚለዉ መከራከሪያ ከራስ ወዳድነት ወይም ከአዛኝ ቅቤ አንጓችነት አስተሳሰብ የዘለለ አይሆንም። በአግባቡ የምገለጽበት የራሴ ቋንቋ እያለ ታሪኬንና ማንነቴን በአግባቡ ሊገልጽ በማይችል በሶስተኛ ወገን ቋንቋ እንዲገለጽ መፈለጉ ምንጬ ለህልዉናዬ ግድ የሌለዉ አስተሳሰብ ከመሆን አያልፍም። ስለዚህም ወጋጎዳ ያነጣጠረዉ በአራቱም ቋንቋዎች ህልዉና ላይ ብቻ ሳይሆን ከላይ በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 39 ስር በተጠቀሱት የብሄሮቹ መሰረታዊ የማንነት መብቶች ህልዉና ላይ በመሆኑ ሀይለኛ

ተቃዉሞ ገጠመዉ። ብሄሮች “ለዚህ ቋንቋ እምቢኝ አንገዛም” በማለት ድምጻቸዉን ጮክ ብለዉ ማሰማት ጀመሩ። ነባር ቋንቋዎችን አጥፍቶ በአሃዳዊ ቋንቋ በመተካት በሂደት ነባር ብሄሮችን እንዳልነበሩ ለማጥፋት ያለመዉ የፖለቲካ ፕሮጀክት ተቀባይነት አጣ። ከዚህ አኳያ ጉዳዩ የፖለቲካ ስህተት ነበር ብሎ መደምደም ይቻላል። ደግነቱ የፖለቲካ ስህተቱ የተፈጠረዉ ለብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች መብቶች ዘብ በቆመዉ በደኢህዴን/ኢህአዴግ የአስተዳደር ስርአትና ዘመን በመሆኑ ችግሩን ለመፍታት አላንገራገረም። የብሄሮቹን እንቢታ በማዳመጥ እና ህገመንግስታዊ ትርጉሙን ከግምት ዉስጥ በማስገባት መጤዉን ቋንቋ ከብሄሮቹ ጫንቃ ላይ ለማንሳት ግድ ሆኖበታል። ወጋጎዳ የዉሃ ሽታ ሆኖ ቀረ። ፖለቲካዊና ህገመንግስታዊ ስህተቱን ግምት ዉስጥ ሳያስገቡ ብዙ ደክመዉ ለፈጠሩት ቡድኖች ጽናቱን ይስጣቸዉ። እስከአሁን ሀዘን ለይ እንደማይሆኑ ተስፋ እናደርጋለን። ይህ ክስተትም የብሄር ፓርቲዎችን ህልዉን በማጥፋት አሃዳዊ ኢህአዴግ ለመፍጠር ፍላጎትና ተልእኮ ያላቸዉ አካላት ቢኖሩ ሊገጥማቸዉ ለሚችለዉ ፖለቲካዊና ህገመንግስታዊ ህጸጽ አይነተኛ ማስጠንቀቂያና ማሳያ ነዉ። የብሄር ፓርቲዎችን ህልዉና ያጠፋ ኢህአዴግ የብሄር ቋንቋዎችን እና በዚህ የሚገለጹ ማንነቶችን ለድርድር ለማቅረብ ዝግጁ የሆነ ኢህአዴግ ነዉ። ስለዚህም ብሄሮች የማንነታቸዉ መገለጫ የሆነዉን ቋንቋቸዉን ለማጥፋት ወጋጎዳን የፈጠሩትን አካላት ወጊድልኝ እንዳሉት ሁሉ በብሄራዊ ድርጅቶች ግንባርነት የተመሰረተን ኢህአዴግ በሚያስቀጥሉ(አዲሱን አስተሳሰብ ወጊድልኝ በሚሉ) እና የብሄሮችን መብቶች ለድርድር ለማቅረብ ዝግጁ በሆኑ የአሃዳዊ ኢህአዴግ አስተሳሰብ በሚያራምዱት ጥቂቶች መካከል ፍጥጫ መፈጠሩ አይቀርም። ስለዚህ ኢህአዴግ ከራሱ ተሞክሮ ፖለቲካዊና ህገምንግስታዊ ስህተት ዉስጥ መግባት የለበትም። የዚህ አስተሳሰብ አራማጆች

ካሉ በብሄር ብሄረሰቦች ጩኸት ከመሸነፋቸዉ በፊት አስፍተዉ እንዲያስቡበት ይመከራሉ።

## “ስልጤ ስልጤ እንጂ ጉራጌ ኣይደለም”

ሌላዉ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ለዚህ ርእሰ ጉዳይ በምሳሌነት ሊቀርብ የሚችለዉ ከዓመታት በፊት በዚሁ ክልል “ስልጤ ስልጤ እንጂ ጉራጌ አይደለም” በሚል መሰረተሀሳብ ላይ ተመስርቶ ከረጅም ጊዜ ትግል በኋላ ድል የተቀዳጀዉ የማንነት ጉዳይ ነዉ። በወቅቱ ክቡር አቶ ሬድዋን ሁሴን እና ምክትላቸዉ ይህን መሰረታዊ ህገመንግስታዊ ጥያቄ ይዘዉ የተነሱት በራሳቸዉ ቋንቋ መጠቀም እና የብሄረሰቡን የራስን እድል በራስ የመወሰን ሁለንተናዊ መብት አይገባችሁም በመባላቸዉ ነዉ። የማንነት ጉዳይ ሊወሰን የሚችለዉ በህዝቡ በራሱ ነዉ። አንድ ህዝብ ወይም የአስተዳደር ስርአት በሌላኛዉ ህዝብ ማንነት ላይ የመወሰን መብትም ስልጣንም አይኖረዉም። ይህን የመብት ጉዳይ ለመወሰን ለማይመለከተዉ ህዝብ የሚሰጥ ፖለቲካዊም ሆነ ህገመንግስታዊ መርህ ቢኖር እርሱ ዲሞክራሲያዊ ህገመንግስት ወይም የፖለቲካ አስተሳሰብ አይደለም። ለዚህም ነዉ ጥያቄዉ ሲነሳ የሚመለከተዉ ብሄር ብቻ በሰጠዉ የህዝበ ዉሳኔ ድምጽ “የህዝብ ነዉ ወይስ የጥቂት ግለሰቦች ጉዳይ?” በሚለዉ ላይ እንዲወሰን የተደረገዉ። ጉዳዩ በአንድ ወቅት በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች መካከል እንደተከሰቱት የአስተዳደር ወይም የመኖሪያ አካባቢን የመወሰን ጥያቄ ቢሆን ኖሮ ዉሳኔ የመስጠት መብቱ በህግ ድምጽ የመስጠት መብት ያላቸዉ የአካባቢዉ ነዋሪ ዜጎች ሁሉ ይሆን ነበር። ባለመሆኑም ዉሳኔ የሰጠዉ ንቅናቄዉን የመራዉ የስልጤን ህዝብ የሚወክለዉ የፖለቲካ ድርጅት እና ብሄረሰቡ እንጂ ክልሉን የሚመራዉ የፖለቲካ ድርጅት እና የክልሉ ብሄር ብሄረሰቦች በሞላ አይደለም። የስልጤ ህዝብ በሰጠዉ ዉሳኔም ጉራጌነቱን ሳይሆን ስልጤነቱን አረጋግጧል። ከዚህ

አኳያ ሲታይ የአሁኑ ኢህአዴግ በስልጣን ላይ ባለበት ሁኔታ ብሄራዊ ድርጅቶችን ያፈረሰ አህዳዊ የፖለቲካ ድርጅት የመፍጠር ሀሳብ ቢቀርብ ዉሳኔዉ የድርጅት አመራሮች ወይም የድርጅቱ አባላት ብቻ አይሆንም። ህዝቡ ኢህአዴግን ወደስልጣን ያወጣዉ ብሄር ብሄረሰቦች አሁን የተጎናጸፏቸዉን ህገመንግስታዊ መብቶች ለድርድር የማያቀርብ የፖለቲካ ድርጅትና አወቃቀር ስላለዉ ነዉ። ደጋግመን እንደገለጽነዉ የተጠቀሱትን መብቶች ለድርድር ለማቅረብ የሚያስችል ክፍት የሆነ በር ያለዉ አህዳዊ ኢህአዴግ የተፈጠረ እለት የህዝቡ ሉአላዊ ስልጣን እንደተጭበረበረ ይቆጠራል። የብሄራዊ ፖለቲካ ድርጅቶችን የወከሉት የክልል ብሄሮች እና ብሄረሰቦች ስልጣናችንን የሰጠነዉ ድርጅት እና ፖለቲካዊና ህገመንግስታዊ ርእዮተዓለሙ ባለመኖሩ ወይም በመንሸዋረሩ የሰጠነዉን ስልጣን ይመለስልን የማለት መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ። ለአሃዳዊዉ ኢህአዴግ ያመች ዘንድ የቋንቋ መብትን ጨምሮ ሌሎች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብቶችን የሚጋፉ አስተዳደራዊና መዋቅራዊ ሁኔታዎች ሲከሰቱም በህዝበ ዉሳኔ በሚሰጥ ድምጽ እንዲወሰን ጥያቄ ማቅረባቸዉ አይቀርም። ስለዚህ ይህ ጉዳይ ተጨፍልቆ በአንድ ላይ የሚታይ ሳይሆን የክልሎች ብሄሮችና ብሄረሰቦች በተናጠል የሚወስኑበት ነዉ። በካርዱ ወደስልጣን ያወጣዉን የገዛ ክልሉን ብሄራዊ ድርጅት "ስመርጥህ ይዘኸዉ ከተነሳኸዉ ዓላማ ዉጭ እየተንቀሳቀስክ በመሆንህ በጉዳዩ ላይ መወሰን ያለብኝ እኔዉ እራሴ ነኝ" ማለቱ አይቀርም። "….ስልጤ ስልጤ እንጂ ጉራጌ አይደለም …." እንደተባለዉ "የትግራይን ወይም የኦሮሞን ወይም የአማራን… ወዘተ የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ያረጋገጠዉ የህወሓት ወይም የኦህዴድ ወይም የብአዴን …ህልዉና እንጂ እርሱን በማጥፋት የተመሰረተዉ ቀድሞ የማላዉቀዉ አሃዳዊ ኢህአዴግ አይደለም፤ ስለዚህ ስልጣኔን መልስልኝ…" የማለት መብቱ የተጠበቀ ነዉ።

የዉህደቱ ጉዳይ ኢህአዴግ ስልጣን ላይ እያለ ቢፈፀም የሚከተለዉ ህዝባዊ አደጋና ህገመንግስታዊ የመብት ጥያቄ ይኸዉ ነዉ።

- የፌዴራሉ መንግስት የቆመዉ ከክልሎች ተቆርሶ በተሰጠዉ ስልጣን ነዉ። የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም ስርአት bottom —up አካሄድን የተከተለ ነዉ። ፌዴሬሽኑ እንዲኖር ከተፈለገ የብሄር ብሄረሰቦችን የራስን እድል በራስ የማስተዳደርና ሉአላዊ የስልጣን ባለቤትነት የሚያስጠብቅ ህገመንግስታዊ መሰረት እና ትግበራ መኖር አለበት። ይህ በሌለበት ሁኔታ ፌዴሬሽኑ አይኖርም። ምክንያቱም ክልሎቹ ለፌዴራል መንግስቱ ስልጣን አይሰጡትምና ነዉ። ህልዉናቸዉን ለማያስጠብቅ ማእከላዊ አካል የሚሆን በዉክልናም ሆነ በሌላ ፖለቲካዊና አስተዳደራዊ ተልእኮ ሚና የሚኖራቸዉን ተወካዮቻቸዉን አዋጥተዉ ለመላክ ፈቃደኛ አይሆኑም። ይህ ሊሆን የሚችለዉ ህገመንግስቱን አሻሽሎ አሁን ካለዉ የተለየ የአስተዳደር መዋቅር ማስፈን ሲቻል ነዉ። ቢሆንም ግን በዚህ የሚያበቃ አይደለም። የፌዴሬሽኑ አባላት ህገመንግስቱ በመሸራረፉ በአባልነት አንሳተፍበትም በመሆኑም የመገንጠል መብታችንን ተግባራዊ እናደርጋለን ሊሉ ይችላሉ። ይህን ጉዳይ ከህገመንግስቱ ድንጋጌ አንቀፅ 46 ጋር አቆራኝቶ ማየት ተገቢ ነዉ። በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 ስር የፌዴራሉ መንግስት በክልሎች የተዋቀረ ስለመሆኑ በግልጽ ተደንግጓል። ክልሎቹም የኢህአዴግን አራት ብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች እና አምስት ብሄራዊ የኢህአዴግ አጋር ድርጅቶችን የፈጠሩት በድምሩ ዘጠኝ ስለመሆናቸዉ ተጠቅሰዋል። ስያሜአቸዉ የትግራይ፣የአፋር፣የአማራ፣የኦሮሚያ ወዘተ በሚል ይገለፃል። ስለዚህ ሲጀመር የክልሎቹ ስያሜዎች የጠቀሷቸዉ ብሄር ብሄረሰቦች መኖር አለባቸዉ። ሲቀጥል የእነዚህ ክልሎች መኖር የብሄር ብሄረሰቦቹን የራስን እድል በራስ ለመወሰን መብት በሚያስጠብቅ አኳኋን ተጠብቀዉ መኖር አለባቸዉ። በሶስተኛ ደረጃ በዉስጣቸዉ ያሉትን ብሄር ብሄረሰቦች ሁለንተናዊ መብቶች የሚያስጠብቅ የፌዴራል መንግስት ፈቅደዉና አምነዉበት ማወቀር አለባቸዉ። ሲጠቃለል ፌዴሬሽኑ እንዲኖርም እንዳይኖርም የመወሰን ሉአላዊ ስልጣን በእጃቸዉ ነዉ። ይህ ከሆነ ደግሞ

አሃዳዊነት ቅርጽ ያለዉ ኢህአዴግ እነዚህን የክልሎች ስልጣናት ሊያሟላ አይችልም። አሃዳዊ ከሆነ ክልሎች በብሄራዊ ድርጅቶቻቸዉ መሪነት አይተዳደሩም። በግልባጩ የብሄር ብሄረሰቦችን ሉአላዊ ስልጣን የሚያስጠብቅ ፖለቲካዊ ሰብእና እና የአከላለል ስርአት አይኖርም። ይህን ጊዜ ከፌዴራል በመለስ ያሉት የመስተዳድር እርከኖች ስልጣን የሚያገኙት ከፌዴራል መንግስቱ ይሆናል። በመብት ሳይሆን በስጦታ መልክ ይንቆረቆርላቸዋል።

## *የመሬት ጥያቄ መሬት ላራሹ በሚለዉ ጠባብ ትርጉም ብቻ የሚታይ አይደለም*

ኢህአዴግ በብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና ላይ ካልተመሰረተ ስልጣን ተቆርሶ አልተሰጠዉም ማለት ነዉ። ይህ ሁኔታ በፌዴሬሽኑ ምስረታ ላይም በቀጥታ ተጽእኖ ይኖረዋል። በኢህአዴግ የፖለቲካ ስልጣን ደረጃም ሆነ በፌዴሬሽን ምስረታ ደረጃ ስልጣን ከታች ወደላይ ሳይሆን ከላይ ወደታች ይሆናል። ኢህአዴግ ይህን ሁሉ የህገመንግስት ድንጋጌ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ካጣ ምን ቀረዉ ሊባል ነዉ? ባዶዉን ቀረ እንጂ! የደርግ ወይም የንጉሳዊ አገዛዝ ስርአቶች ተመልሰዉ መጡ ማለት ነዉ። ከ25 ዓመታት በፊት የነበሩት የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጥያቄዎች አገረሸባቸዉ ማለት ነዉ። ከ25 ዓመት በፊት የነበሩት ጥያቄዎች በመሰረቱ ሶስት ናቸዉ። የመሬት ፣ የዲሞክራሲና የብሄር ጥያቄዎች ናቸዉ። በበኩላችን የመሬት ጥያቄ መሬት ላራሹ በሚለዉ ጠባብ ትርጉም ብቻ የሚታይ አይደለም። ምክንያቱም የደርግ መንግስት የመሬት ላራሹን ጥያቄ ለስም ያህል ምላሽ ሰጥቶበታል። ቢሆንም ግን ከመሰረታዊ መብቶች መሰረተሃሳብ አንፃር ሲዳሰስ በተግባር አልተመለሰም። በመጀመሪያ ደረጃ አርሶ አደሩ ያመረተዉ ምርት በሙሉ ነፃነት ተጠቃሚ አልነበረም። በኮታና በተለያዩ ምክንያቶች የምርቱ ነፃ ተጠቃሚ አልነበረም። ማለትም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ እና ከእርሱ ዉሳኔ ዉጭ በሆነ ተፅእኖ ምርቱን እንዲሸጥ ከተገደደና ከተወሰደበት የኢኮኖሚ መብት

ነፃነቱን ሙሉ ለሙሉ ተነጥቆ ነበር። ዋነኛዉና መሰረታዊ ጭቆናዉ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች በራሳቸዉ ጉዳይ ላይ እራሳቸዉ እንዲወስኑ የሚያስችል ስልጣንም ሆነ መብት አልነበራቸዉም። ይህም ከመሬት ተጠቃሚነት ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ አለዉ። እራሱን በራሱ እና በሚያመቸዉ መንገድ የማስተዳደርና በሚመለከቱት ጉዳዮች ላይ የመወሰን ስልጣን ያልተሰጠዉ ብሄር ብሄረሰብ በሀብቱ የመጠቀምና የመልማት መብቱን ተነፍጓል ማለት ነዉ። ሀብትና የመልማት መብት ሲባል ደግሞ መሬትንና መሬትን ተጠቅሞ የመልማት መብትን ያካትታል። ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ መብትና ስልጣን በአሃዳዊዉ እና ለብሄር ብሄረሰቦች ህልዉና እዉቅና ባልሰጠዉ ደርግ ልኡካን እጅ እንጂ በብሄር ብሄረሰቦች እጅ አልነበረም። በመሆኑም የመሬት ላራሹ ጥያቄ ከብሄር ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት በተለይ ደግሞ የራስን ሀብት ተጠቅሞ ከመልማትና በራስ አስተዳዳሪዎች ከመወሰን መብት አንጻር ሲታይ ምላሽ አላገኘም ነበር። የብሄራዊ ጭቆናዉም ጉዳይ ከዚሁ ጋር ተሳስሮ የሚታይ ነዉ። ስለዚህ ኢህአዴግ የደርግ ስርአተን ገርስሶ ይህን የብሄር ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን መብት በተግባር የሚያረጋግጠዉን የአከላለል ስርአትና በክልሎች ሉአላዊ ስልጣንነት የተዋቀረዉን ፌዴሬሽን ማስቀጠል ከፈለገ መጀመሪያ በዉስጡ የብሄራዊ ድርጅቶችን ህልዉና ማስቀጠል ይጠበቅበታል። ለዚህ ሀሳብ እንዲያግዘን በኢፌዴሪ ህገመንግስት ደንጋጌዎች ይዘትና ተልእኮ ላይ የተሻለ እዉቀት ያላቸዉን የዶ/ር መንበረፀሀይ ታደሰን አጭር ነገር ግን ሰፊ ሀሳብ የያዘ አገላለጽ እንጥቀስ። እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል።

## ዶ/ር መንበረፀሀይ ታደሰ

*"....ለብሄረሰቦች እዉቅና ከሰጠን እና ብሄር ብሄረሰቦች እራሳቸዉን በራሳቸዉ እንዲያስተዳድሩ ህገመንግስታዊ መብት ከሰጠናቸዉ መልከአምድራዊ ፌዴራሊዝም ቦታ*

*አይኖረዉም…ምክንያቱም እያንዳንዱ ብሄር ማንነቱ፣ ታሪኬ ፣ ቋንቋዬ አንድ ነዉ ብሎ የሚያስብ ህብረተሰብ ራሱን የሚያስተዳድርበት የመንግስት አወቃቀር መፍጠር ያስፈልጋል ህገመንግስቱ ያደረገዉ ይህንን ነዉ……"*

የአሃዳዊ ኢህአዴግ ተፈጥሮ ደግሞ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ዶ/ር መንበረ የገለጹትን አይነት የመንግስት አወቃቀር እንዲኖር ላያስገድድ ይችላል። በዚህ ህገመንግስታዊ መርህ ካልተገደደ ደግሞ በአጠቃላይ ለህገመንግስቱ ህልዉና እንደዚሁም ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በህገመንግስቱ የተጎናጸፏቸዉን መብቶች እንዳይሸራረፉ ለ25 ዓመታት ዘብ የቆመዉ ኢህአዴግ አስተሳሰብ ተቸንፏል። ከተቸነፈ ደግሞ ለብሄር ብሄረሰቦች መብትና ማንነት መቸነፍና መጥፋት የሚሰራ የፖለቲካ ድርጅት ሆኗል። ይህ ከሆነ ዘንዳ ብሄር ብሄረሰቦች አሃዳዊ ኢህአዴግ እንኳንስ በምርጫ ካርድ በጉልበትም ቢመጣባቸዉ አይቀምሱትም። "አንድም ለኛ ስትል ጣፍጥ አለያም ልክ እንደሌሎቹ ዳግም ላትመለስ ከቀያችን ኣናደርስህም" ማለታቸዉ አይቀርም።በዚህ ጽሁፍ የተለያየ ክፍል ዉስጥ እንደተጠቀሰዉ አህዳዊ ፖለቲካ አወቃቀር ያለዉ የፖለቲካ ድርጅት በአንቀጽ 46 ስር "ክልሎች የሚዋቀሩት በህዝብ አሰፋፈር፣ በቋንቋ ፣ማንነት እና ፈቃድ ላይ በመመስረት ነዉ…" ከሚለዉ ድንጋጌ ጋር ሊጣጣም አይችልም።በራሱ የፖለቲካ ድርጅት ዉስጥ ብሄር ብሄረሰቦችን መሰረተ ያደረገ የዉክልና ስርአት የማያስተናግድ የፖለቲካ ድርጅት በብሄር ብሄረሰብ አሰፋፈር ላይ የተመሰረተ የአከላለል ስርአት እንዲኖር በቅድመሁኔታነት የሚያስቀምጥ የፖለቲካ ርእዮተዓለም እንዲኖረዉ አይገደድም። የፖለቲካ ድርጅቱ የሚመሰረተዉ በሀገራችን በሊብራል ዲሞክራሲ አስተሳሰብ በግለሰብ መብት ላይ ብቻ ተመስርተዉ እንደተዋቀሩት የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ነዉ። የድርጅቱ አባል ለመሆን መስፈርቱ ግለሰብ መሆን እንጂ የብሄር ማህበራዊ መሰረት አይሆንም። ፓርቲዉ የሚዋቀረዉ በዚህ አስተሳሰብ ከሆነ የአከላለል ስርአቱም በየትም ቦታ የእነዚህን ግለሰቦች ፖለቲካዊ መብት በየትም ቦታ ማስተናገድ የሚችል እንዲሆን ይጠበቃል። ይህ እንዲሟላ ደግሞ የቋንቋ ጉዳይ በማእከላዊዉ

ፖለቲካ ድርጅት እና መንግስት እንጂ በብሄራዊ ፖለቲካ ድርጅት ወይም ከፌዴራል መንግስት በመለስ ባለ አስተዳደራዊ አካል የሚወሰንበት ስርአት የመኖሩ ጉዳይ እጅግ የጠበበ ነዉ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ብሄር ብሄረሰቦች ማንነታቸዉን መሰረት አድርገዉ የመወሰን መብታቸዉ የጠበበ ይሆናል። ምክንያቱም የሚዋቀሩት አስተዳደራዊ ክልሎች በተማከለ የፖለቲካና የአሰተዳደር አስተሳሰብ ላይ ስለሚመሰረቱ ገዥ ዉ ጉዳይ የነባሩ ብሄረሰብ(indigenous) ማንነት፣ቋንቋ ወዘተ መብት ሳይሆን የግለሰብ መብት ጉዳይ ነዉ። በህገመንግስታችን ልዩ ትኩረት የተሠጠዉ የቡድን መብት በተማከለዉ አስተሳሰብ እና አሃዳዊ ስርአተመንግስት አስተሳሰብ ተጽእኖ ምክንያት ቦታ አይኖረዉም። ስለዚህ አንቀጽ 46 በተግባር የማይተረጎም ከሆነ ህልዉናዉ አደጋ ላይ ይወድቃል።

## ከማጥፋቱ በፊት መጥፋቱ አይቀርም። ይገባዋልም።

የፌዴራል መንግስት አባላትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ያካተተዉ የኢፌዴሪ ህገመንግስት አንቀጽ 47 ንኡስ አንቀጽ ሁለት በንኡስ አንቀፅ አንድ በተመለከቱት ዘጠኝ ክልሎች ዉስጥ የተካተቱት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች በማንኛዉም ጊዜ የራሳቸዉን ክልል የማቋቋም መብት እንዳላቸዉ ያስረዳል። አሁን ያሉት ክልሎች የተመሰረቱት ይህን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ ነዉ። በተመሳሳይ ሁኔታም በእያንዳንዱ ክልል ዉስጥ ያሉት ብሄሮች የራሳቸዉን እድል በራስ የመወሰን መብታቸዉን ተጠቅመዉ አካባቢያቸዉን የማስተዳደር፣ በመረጡት ቋንቋ የመጠቀም፤በመረጡት የአካባቢዉ ነዋሪ ተምጭ መተዳደር፤ አስፈላጊ ነዉ ብለዉ ባመኑ ጊዜም ህገመንግስታዊ ስርአቱ በሚፈቅደዉ መሰረት የራሳቸዉን አካባቢያዊ ክልል የማቋቋም መብታቸዉ የተጠበቀ ነዉ።በአንድ በኩል ነባሩንና እነዚህን መብቶች ለማስጠበቅ የታገለዉን የብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና ፍጥረት

የሆነዉን  በሌላ በኩል ደግሞ የብሄራዊ ድርጅቶችን ህልዉና ያጠፋ አህዳዊ ኢህአዴግን  ከዚህ ድንጋጌ ጋር አስተሳስሮ ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል። አሃዳዊ የኢህአዴግ ፓርቲ ለብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና እዉቅና አይሰጥም። ለብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና እዉቅና የማይሰጥ የፖለቲካ ድርጅት በዘጠኙም ክልሎች ዉስጥ የሚኖሩ ብሄሮች፤ ብሄረሰቦችና ህዝቦች በራሳቸዉ ጉዳይ ላይ ሉአላዊ ስልጣን እንዲኖራቸዉ የማድረግ ድርጅታዊ ተፈጥሮ፤ተልእኮና የአባልነት መሰረት አይኖረዉም። የአባልነት መሰረቱ የግለሰብ መብት እንጂ ብሄራዊ ማንነት የወለዳቸዉ ብሄራዊ ድርጅቶች አይደሉም። ስለዚህም በአስተዳደራዊ መዋቅርና በህዝቦች ሉአላዊ ስልጣን ላይ የሚኖረዉ ጽንሰሀሳብ ብሄር ብሄረሰቦችን ሳይሆን ግለሰብን ብቻ ማእከል ያደረገ  የአህዳዊ ስርአተ መንግስት አስተሳሰብ ነዉ። በመሆኑም እንኳንስ ልክ እንደስልጤ ብሄር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የራስን ክልላዊ አስተዳደር የመቀዳጀት እና ሌሎች በየራስን እድል በራስ የመወሰን ጽንሰሀሳብ ዉስጥ የሚካተቱትን የብሄር መብቶች ሊያስጠብቅ ይቅርና አሁን ያሉት ዘጠኝ ክልሎች ህልዉናን ለማስጠበቅ የሚያስችል ተፈጥሮ አይኖረዉም። ስለሆነም የአንቀጽ 47 ድንጋጌዎች ህልዉና በአሃዳዊዉ ኢህአዴግ ጥያቄ ዉስጥ መዉደቃቸዉ አይቀርም። ይህንን የብሄሮች፤ብሄረሰቦችና ህዝቦች መብት በአስተማማኝ ሁኔታ የማያስጠብቅ ፖለቲካ ድርጅት ወይም አስተሳሰብ ደግሞ ከማጥፋቱ በፊት መጥፋቱ አይቀርም። ይገባዋልም።የዚህ ጽሁፍ መሰረታዊ ዓላማም በጥቂት ቡድኖች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ አህዳዊ ኢህአዴግ  እዉን ሆኖ ጥፋት ከመፈጸሙ በፊት ድጋፍ በማሳጣትና አስተሳሰቡን በማምከን ከወዲሁ እንዲጠፋ ለማድረግ ነዉ። የነባሩ ኢህአዴግ ተልእኮ ግን በብሄር ብሄረሰቦች ሉአላዊ ስልጣን ህልዉና ላይ የተመሰረቱ ብሄራዊ ድርጅቶች ድምር ዉጤት የሆነዉን ዓላማ ማሳካት ነዉ። ብሄራዊ ድርጅቶቹ በቅድሚያ የሚወክሉትም በሚወክላቸዉ ክልልሎች ያሉትን ብሄር ብሄረሰብና ህዝቦች ሉአላዊ ስልጣን

ነዉ። ይህን ወደጎን የተወ ሀገራዊ ተልእኮና የፖለቲካ አወቃቀር የጋራ ጥቅምንና የብሄር ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን ሉአላዊ ስልጣን ስለማያስጠብቅ ለአንቀጽ 47 ህልዉና እና ተግባራዊነት ይታገሉለታል። ስለዚህም አንቀጽ 47ም እንዲኖር እና በዉስጡ የያዛቸዉ ተልእኮዎች ተግባራዊነት እንዲቀጥሉ ከተፈለገ በብሄራዊ ድርጅቶች ህልዉና ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅት ስልጣን መያዝ የግድ የሚል ሆኖ እናገኘዋለን።

*"የፈራ ይመለስ"*




*ከዳዊት ጸሃየ የተወሰደ*

ከዚህ በላይ በምትመለከቱት የአንበሳ ምስል ላይ ተምሳሌታዊ ጥያቄና መልስ ሰፍሯል። በበኩላችን ከአንበሳ ይልቅ ንብ ቢሆን እንመርጥ ነበር።በተግባርም በዉክልናም በአግባቡ የሚወክለን ንብ በመሆኑ ነዉ። ከእንበሳዉ ጋር ጠብ

የለንም። ጠብ ሊኖረን የሚችል ከሆነም ባለፉት ዘመናት አንበሳዉ ይወክላቸዉ ከነበሩት ስርአቶች እና ከፈጸሟቸዉ ተግባራት ጋር ነዉ። እጅግ የምናከብራቸዉና ሲያስተላልፏቸዉ ከነበሩት ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች ሳንከፍልበትና በርቀት ሆነን የታነጽንባቸዉ የቀድሞዉ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ "…የኢትዮጵያ አየር መንገድ አርማ ለምን ተቀየረ…" ተብለዉ ሲጠየቁ የመለሱትም ይህንኑ መሰለን። መልሳቸዉ "… ከአንበሳዉ ጋር ጠብ የለንም…." የሚል ይዘት ነበረዉ? ከተሳሳትን እንታረማለን። የሆነ ሆኖ በአንበሳዉ ላይ ከቀረበዉ መልእክት እንጀምር።

ጥያቄ- "ስማ እንጂ አንበሳ ከትግራይነትህና ከአነበሳነትህ አንዱን ምረጥ ተብለህ ብትጠየቅ የቱን ትመርጣለህ?"

መልስ-"ጥያቄአችሁ የሚመለሰዉ በጥያቄ ነዉ። አንበሳነቴ ነዉ ትግራይ እንደሆን ያደረገኝ ወይስ ትግራይነቴ ነዉ አንበሳ እንድሆን ያደረገኝ?"

"ግንባር ወይስ አሃዳዊ ፓርቲ?" የሚል ጥያቄ ይዘን የቀረብነዉም በዚህ አስተሳሰብ ነዉ። በዚህች አገር ረጅም ዓመታትና ስፍር ቁጥር የሌላቸዉን የብሄር ብሄረሰቦችንና ህዝቦችን መስዋእት ያደረገዉ ትግል አንዱ ምክንያት " ….አንተነትህ አንተነትህን ሳይሆን እኔነቴን ብቻ እያሰተጋባና ስለኔ ህልዉና ብቻ እየገለጸ ሊኖር ይገባል….ያንተ ማንነት እራስህን ሳይሆን እኔን ብቻ ዲፉይን እያደረገ ሊኖር ይገባል። ይህ እንዲሆን ደግሞ ታሪክህ፣ቋንቋህ፣ባህልህና ማህበራዊ መሰረትህ በአጠቃላይም ይህን ሁለንተናዊ መብትህን የሚያስጠብቅ ሉአላዊ ስልጣን ሊኖርህ አይገባም …." የሚለዉን አስተሳሰብ በመገርሰስ የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች አገር የሆነች አዲስ ኢትዮጵያን ለመመስረት ነዉ። ስለዚህም በኢትዮጵያዊነታችን የምንኮራዉና በፍቅር የምንኖረዉ ትግራይ፣ኦሮሞ፣ወላይታ፣አማራ፣ሱማሌ፣ጋምቤላ ወዘተ የመሆናችንን ተፈጥሮአዊ መብታችንን የምታስጠብቅልን ኢትዮጵያ እና

ስርአተ መንግስት ሲኖር ብቻ ነዉ። ፍርጥርጥ አድርጎ መነጋገር የማይወዱ እንዳሉ ብንገነዘብም በትግሉ ወቅት የተነገረን አንድ አባባል እንጠቀም። አንድ ታዋቂ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በህይወት የሌለ የህወሓት ታጋይ ከኢትዮጵያ ዉጭ ሆኖ(በትግሉ ወቅት) ባደረገዉ ክርክር "...ለትግራይ ህዝብ ያልሆነች ኢትዮጵያ ትበጣጠስ..." ያለዉን ልብ ይሏል። እዉቁ ታጋይ ይህን ያለዉ እየታገለላት በነበረዉ ኢትዮጵያና ብሄር ብሄረሰቦቿ ላይ ክፉ ምኞትና ተልእኮ ስለነበረዉ አይደለም። ኢትዮጵያ ለትግራይ ህዝብ ጥቅም ብቻ መኖር አለባት ለማለት ፈልጎም አልነበረም።ለብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት ህይወቱን ለመስጠት የወሰነ ታጋይ ስለትግራይና ስለህዝቧ ጥቅም ብቻ ያስባል የሚል ካለ እርሱ የፖለቲካ እዉቀት የሌለዉ ነዉ። የህወሓትና የአጋሮቹ የትግል ዉጤት በአዲሲቷ ኢትዮጵያ እዉን እንዲሆን ያደረገዉም የሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና የጋራ ተጠቃሚነት ነዉ። ስለሆነም በወቅቱ ይህን አባባል መሰረት አድርጎ የቀረበዉ ትችት ፍጹም ስህተትና አሁን በተግባር የተረጋገጠዉን የህወሓትን የትግል ዓላማ በቅጡ ካለመረዳት የመነጨ ነበር። የአባባሉ መልእክት "...ሁላችንም በእኩልነት የማንታይባት ኢትዮጵያ ሰላም አይኖራትም። የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ማንነት እኩል እዉቅና እና መብት ያልተጠበቀባት ኢትዮጵያ ይህን መብት ለማስጠበቅ ሲባል ከሚደረግ ጦርነት ያለፈ ታሪክ አይኖራትም።.........።ስለዚህ ኢትዮጵያን እንድንወዳትና እንድናፈቅራት ከተፈለገ የፖለቲካ ስርአቷ የእያንዳችንን ህልዉና ሊወድና ሊያፈቅር ይገባል...." ከሚል መሰረታዊ ጭብጥ የመነጨ ነዉ። ስለዚህም ትግራይ እንድሆን ያደረገኝ አንበሳነቱ(ኢትዮጵያዊነቱ) አይደለም። ትግራይነቱ ስለተከበረልኝ ነዉ አንበሳነቱን(ኢትዮጵያዊነቱን) እንድወድ ያደረገኝ። መጀመሪያ በኢትዮጵያ ዉስጥ የተገኘሁት ትግራይ ከሚባል ህብረተሰብ እና ወላጆች ተፈጥሬ ነዉ። ምንጨ እና ታሪኬ ባልተጠበቀበት ሁኔታ በሌሎች ምንጭና ታሪክ ልኮራም ልደሰትም

አልችልም። ኢትዮጵያዊነቴ የሚያኮራኝ በሌሎች ታሪክና ማንነት ጥገኛ ሆኜ ሳይሆን በራሴ ማንነት ላይ ተመስርቼ ነዉ። ይህን አመክንዮ በመንተራስም ኢህአዴግ እንድንሆን ያደረገኝንየትግራይ ብሄር ብሄረሰቦችን ማንነት የሚያስጠብቀዉ የህወሓት መኖር ነዉ። ኢህአዴግ እንድንሆን የሚያደርገን ህወሓትነታች ነዉ። መጀመሪያ ኢህአዴግ ከሆንን ህወሓት የሚባል የፖለቲካ ድርጅት አይኖርም። ህወሓት በሌለበት ሁኔታ ደግሞ የትግል ዉጤት እና ለብሄር ብሄረሰቦች መብቶች መከበር የመሰረት ድንጋይ የሆኑት የኢፌዴሪ ህገመንግስት ድንጋጌዎች አደጋ ላይ ወድቀዋል ማለት ነዉ። ይህ አመክንዮም ለሌሎቹ ብሄራዊ ድርጅቶች ይሰራል። ስለዚህ መጀመሪያ ኢህአዴግ የመሆናችን ጉዳይ ትግራይነታችንን ጥያቄ ዉስጥ ያስገባዋል። ስለሆነም ኢህአዴግ እንድንሆን ከተፈለገ ህወሓት የመሆን መብታች ይጠበቅልን። መነሻዉ ከሌለ መድረሻዉ አይኖርም። በዚህ አስተሳሰብ ለመታገል የሚፈራ ካለ ይመለስ! ምክንያቱም እንኳንስ ስለሌላዉ ህዝብ ስለራሱም ጥብቅና የመቆም ጥንካሬ የለዉምና ነዉ!

## “….እኛ የኢትዮጵ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች….”

ከኢፌዴሪ ህገመንግስት አንፃር “….እኛ የኢትዮጵያ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች….” ማለት፡-

- ሉኣላዊ ስልጣን የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ነዉ ማለት ነዉ፤
- ህገመንግስታችን እንደግለሰብ መብት ሁሉ ለቡድን እና ለብሄሮች መብትም እኩል እዉቅና ሰጥቷል ማለት ነዉ፤
- አሃዳዊ የመንግስት አወቃቀር እና በግለሰብ መብት ላይ ብቻ መሰረት ያደረገ ህገመንግስትና የፖለቲካ አስተሳሰብ ለብሄሮች እና ለቡድኖች የማይሰጣቸዉን መብቶች በአንፃሩ ያጎናፀፈ መሆኑን የሚያስረዳ መሪ ቃል ነዉ፤

- በጥቅሉ ብሄር ብሄረሰቦች ህልዉናቸዉ የታወጀበት እና ይህን ህልዉና ሊፈታተን የሚችል ፖለቲካዊ፣ ህገመንግስታዊና አስተዳደራዊ ስርአትና አወቃቀር ቦታ የሌለዉ መሆኑን ከወዲሁ የሚስገነዝብ ነዉ።

እነዚህ ጽንሰሃሳቦች ሲረጋገጡ ሌሎቹ በዚህ ህገመንግስት መግቢያ ላይ የተካከቱት መሰረታዊ ጉዳዮች ይከተላሉ። የብሄር ብሄረሰቦች መብትና ህልዉና ሲረጋገጥ፡-

- በጋራና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት እየተጠናከረ ይሄዳል፤
- የመብት ረገጣ ጥያቄዎች እንደቡድን ወይም እንደ ብሄር ወይም ብሄረሰብ ጥያቄ የሚቀርብባቸዉ ጉዳዮች አይሆኑም። ስለማይሆኑም በሀገራችን ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለዉ ዲሞክራሲ እየተጠናከረ ይሄዳል፤
- ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለዉ ዲሞክራሲ የተጎናፀፈች ኢትዮጵያን ማረጋገጥ ከቻልን ታሪካችን ማንነትንና ሌሎች መብቶችን ለማረጋገጥ ሲባል በሚፈጠሩ አለመግባባቶች ሳቢያ የኋሊት የምንሄድበት ሳይሆን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገታችን የሚፋጠንበት ታሪክ ይሆናል፤
- የመልማት መብታችንን እና በየአካባቢያችን ያለዉን ሀብት ተጠቅመን በሁሉም አካባቢዎች ተመጣጣኝ እድገት ለማረጋገጥ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል ማለት ነዉ፤
- እነዚህና ሌሎች የብሄር ብሄረሰቦች መሰረታዊ መብቶች የተረጋገጡባት ኢትዮጵያ ስትፈጠር በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ይገነባል፤
- ይህን የሚያሰፍነዉ ደግሞ በብሄር ብሄረሰቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት ላይ የተመሰረተ ህገምንግስታዊና አስተዳደራዊ ስርአት ለማስፈን የማያስችልን በአሃዳዊ አወቃቀር እና በግለሰብ

መብት ቅኝት(ብቻ) የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅት ሳይሆን በብሄራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች ህልዉና እና ምሰሶ ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ድርጅት ብቻ ነዉ

- ስለዚህም *"....እኛ የኢትዮጵ ብሄሮች ብሄረሰቦች ህዝቦች...." ጡራት፣*በመፈቃቀድና በፍቅር ላይ ተመስርተን በአዲሲቷ ኢትዮጵያ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ የምንመሰርተዉ ህልዉናችንን የሚያረጋግጥልን ህገመንግስታዊ፣ርእዮተዓለማዊ እና አስተዳደራዊ የፖለቲካ አስተሳሰብና አደረጃጀት ያለዉ ፓርቲ ሲመራን ነዉ። አንድ የኢኮኖሚ እና የፖለቲካ ማህበረሰብ ማለት ደግሞ ብሄር ብሄረሰቦች በህገመንግስቱ የተደነገጉላቸዉ ሁለንተናዊ መብቶችና ነፃነጾች በእኩልነት መረጋገጡ ሲረጋገጥ ነዉ። ምክንያቱም ይህ መብት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ መንገዳችን ወደአብሮነት ሳይሆነ ወደመለያየት እንዲያመራ ግድ የሚሉ ጭቆናዎች ስለሚከተሉ ነዉ

እናስ? እናማ አሃዳዊ ኢህአዴግን ማሰብ የብሄር ብሄረሰቦች የትግል ዉጤት በሆነዉ በአሁኑ ኢህአዴግ መቃብር ሳቢያ ሊከሰት የሚችለዉን የመጪዉ ዘመን የቀዉስ ታሪክ ለመስተናገድ የቆረጥን እለት ነዉ። እኛ ደግሞ የህወሓት/ኢህአዴግ ልጆች ነን። ዳግም በኢትዮጵያ ምድር ይህን ታሪክ ሊያስከትል የሚችል የፖለቲካ ድርጅት እንኳንስ አባል ልንሆንለት እንዲያስተዳድረንም ድምጽ አንሰጥበትም። ስለዚህም የዚህን አስተሳሰብ ተሸካሚዎችና መሃል ሰፋሪዎች ከወዲሁ በመታገል እነርሱን ሳይሆን አስተሳሰባቸዉን በማራገፍ እንዲፀዱና አብረን እንድንቀጥል እየታገልናቸዉ ነዉ። *ሰላም!*